# ሱሰኛው ፀረ - ኢትዮጵያ ተቋም ምን እያለ ነው?

ቶሎሳ ኡርጌሳ

utolosa@yahoo.com

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ (ይቅርታ ተሟጋች ነኝ ባዩ) ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ዳራ ቢጤን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ምግባሩ ይበዛል፡፡ ህልቆ መሳፍርት ነው። ተቋሙ በተለያዩ ጊዜያት በሚያወጣቸው ግልብ ዘገባዎች የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝብ መልካም ገፅታዎች ለማጠልሸት ያላደረገው ነገር በጣት የሚቆጠር ነው፡፡ ይሁንና ድብቅ አጀንዳውና ፍላጎቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግልፅ እየሆነ በመሄዱ የዘወትር ከንቱ ዳዊቱን አድምጦ ከጎኑ የሚቆም ሀገር ወዳድ ዜጋም ይሁን የዓለም አቀፍ ማህብረሰብ አልተገኘም—መድረክ ከተሰኘ "ሆድ አደር" ፓርቲ በስተቀር። በለተይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የተቋሙ ህቡዕ ዓላማ አግጥጦ እየወጣ በመምጣቱ የዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍን የመሳሰሉ ታላላቅ ተቋማት እርሱ ያወራውን ነገር እንዳልሰማ ማለፍ ጀምረዋል፡፡

እርግጥም የተቋሙ ሰለባ ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም፡፡ ለአጀንዳው ምቹ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መደላድሎችን (enabling environments) ለመፍጠር ፈቃደኛ ያልሆኑ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ታዳጊ ሀገራት ሁሉ ከሰርክ የጥፋት ዘመቻው አልዳኑም፡፡ ታዲያ ይህ ተቋም ፀረ-ኢትዮጵያ ሰብካውን የመጥኝ ያለው ያለ ምክንያት አይደለም– እንጀራው ስለሆነ እንጂ፡፡ ምንያቱም በሚሊዮን የሚቆጠር ረብጣ ዶላር የሚቆርጥለት በሰራው ልክ በመሆኑ ነው። እናም የኒዮ - ሊበራሊዝም አስተሳሰብን የማይቀበሉ አሊያም የርዕዮተ - ዓለሙ አቀንቃኞች ያስቀደዱላቸውን የፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ ጥብቆ ለማጥለቅ ፈቃደኛ ያልሆኑ ታዳጊ ሀገራትን በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ተጠልሎ ሲያወግዝና ከለጋሽ ሀገራት ጋር ያላቸውን ወዳጅነት የሚያጠለሹ ብዕርና ሆድ ወለድ ዘገባዎችን ሲያረግብ እነ ዲታው ጆርጅ ሶሮስ እጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ ይከቱለታል፡፡ ይህን ለማግኘት ደግሞ ቢሳካለትም ባይሳካለትም  የውሸት ዘገባዎችን መወሸከት ስራዮ ብሎ ተያይዞታል፡፡

እንደሚታወቀው ታዳጊ ሀገራት ያልተነካ ግዙፍ ሀብት ባለቤቶች ናቸው። ርካሽ የሰው ጉልበትና ያልተበላ ድንግል መሬት አላቸው። የተፈጥሮ ሃብትና ማዕድኖቻቸውም የሚያስጎመጁ ናቸው። እናም ይህን የተትፈረፈ ሀብት ለመቀራመት ብቸኛውና ምቹው አማራጭ ለዘመኑ እንደማይበጅ በተፈጠረባቸው ሀገራት ጭምር የተመሰከረበት የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ- ዓለም ነው፡፡ ኒዮ - ሊበራሊዝም በራሳቸው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና በማደግ ላይ የሚገኙትን እንደ ኢትዮጵያ፣ ህንድንና ቻይናን የመሳሰሉ ሀገራትን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ይህም ከርዕዮተ-ዓለሙ አቀንቃኞች ጋር ሆድና ጀርባ እዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ እናም ነገሩ "የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል" እንዲሉት በመሆኑ፤ ግዙፉን ሀብታቸውን ላለማስመዝበር 'አሜን' ብለው

ባለማጎብደዳቸው ከፅንሰ- ሃሳቡ መስራቾችና ከባለረብጣዎቹ እንዲሁም ከተላላኪዎቻቸው ጋር አይግባቡም፤ሊግባቡም አይችሉም።

በመሆኑም የአሰተሳሰቡ አራማጆች በውኃ ቀጠነ ዓይነት ክስ ታዳጊ ሀገራትን ያብጠለጥላሉ፤ አንገት ለማስደፋትና ለመማረክ ይደክማሉ፡፡ ከመሬት ተነስተው ያለምክንያትም ይከሷቸዋል፡፡ ከዓለም አቀፍ ማህብረሰብና ከለጋሽ ድርጅት ጋር ያላቸውን ቅርርብ በማበላሸትም የብድርና የዕርዳታ ድጋፍም እንዲያቋርጠባቸው ጠዋት ማታ ይወተውታሉ፡፡ ይህ ትዕይንታቸው ድሮም ዘንድሮም ምናልባትም ወደፊት ከትውልድ ጋር አብሮ የሚዝለቅ የሰው ልጆች የቼዝ ሊሆን ይችላል - የሰው - ለሰው - በሰው 'ጨዋታ' ፡፡ ያ ማለት ግን ጨዋታው ቀጥተኛ ነው እያልኩ አይደለም– ስውር እንጂ፡፡ እነ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ነን ባዮች ዙሪያ ጥምጥም የሚጫወቱት ድብብቆሽ፡፡ የዚህ ድብብቆሽ ጨዋታ ሰላባ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የአፍሪካ ሀገራት ናቸው።

ይህን ጨዋታ ለመከወንም የኒዮ - ሊበራሊዝም አቀንቃኞች በሰብዓዊ መብት ስም ባቋቋሙትና ቀለብ ሰፍረው ወደ ምድረ-አፍሪካና ላቲን አሜሪካ በሚያሰማሯቸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተብዬዎች ዓይነት አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓቾች አማካኝነት የተቀለመዱ ጉንጭ አልፋ ክሳቸውን ያኈጎደጉዳሉ፡፡ ከእነዚህ የሰብዓዊ መብት አቀንቃኞች ውስጥ ስሙና ምግባሩ ለየቅል የሆነውና በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ሱስ የተለከፈው ሂዩማን ራይትስ ዎች አንዱ ነው። ታዲያ የዚህ ተቋም ሰሞነኛው ፀረ - ኢትዮጵያ ክስም ያው የተለመደው የጅል ለቅሶው አካል ወይም ቀጣይ ክፍል ነው ማለት ይቻላል–በተገኘ አጀንዳ ላይ ቁጢጥ እያለ ሀገራችንን የማጠልሸት አባዜ።

እናም ከመሰንበቻው ተቋሙ የሃይማኖት አክራሪነት ጋር በተያያዘ ለፍርድ የቀረቡት ሙስሊሞች ጉዳይ ፍትሃዊነት የጎደለው መሆኑን ጠቅሶ የሰብዓዊ መብት መጣሱን የሚተነትን መግለጫ አውጥቷል፡፡ የፍርደ ገምድሉንና የማን አለብኝ ባዩን ድርጅት ቃል ልዋስና "የፍርድ አሰጣጡ ሂደት ፍትህ የጎደለው ነው" ሲልም ለፍፏል፡፡ ዛቻ ይሁን ምልጃ ባልለየለት መግለጫው የኢትዮጵያ ሙስሊም ሰልፈኞች ሚዛናዊ ላልሆነ የፍርድ መጋለጣቸውንም አራግቧል፡፡

የተቋሙ ችኩልና ብስለት የጎደለው ትንታኔ የተጠርጣሪዎች ቤተሰቦች፣ መገናኛ ብዙሃንና ገለልተኛ ታዛቢዎች ጉዳዮን የሚከታተሉበት ፍቃድ እንዲሁም ይፋ የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት መድረክ እንዲፈጠር ጠይቋል – ኧረ አስጠንቅቋል ቢባል ሳይሻል አይቀርም፡፡ የተከሳሾች የፍርድ ሂደት እንደሚያሳስበው "ያነባው" ተቋሙ፤ የኢትዮጵያ መንግስት የፀረ - ሽብርተኝነት ህጉን በመጠቀም የእምነት ነፃነታቸው እንዲከበር በጠየቁ የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ክስ መመስረቱን አጣጥሏል፡፡ የድርጅቱ ፀረ- ኢትዮጵያ ሱሰኝነት በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም– የፍርድ ሂደቱ ፍትሃዊነት የጎደለው መሆኑንም ከችሎቱ ቀድሞ ደምድሟል፡፡

ታዲያ ይህ የተቋሙ ፈጣን ግልብ ፍረጃ አንድ የሀገሬን ብሂል አስታወሰኝ– “ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ” የሚባለውን፡፡ የተጠርጣሪዎቹ ሰላማዊነት አሊያም ወንጀለኝነት ገና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ድርጅቱ ቀድሞ ነጻ መሆናቸውን ያለምንም ማቅማማት መመስከሩ፤ ሁለት ነገሮችን ያመላክታል–አንድም ማን አለብኝ ባይነቱን ሲሆን፤ ሁለትም ደግሞ ለሰብዓዊ መብት ቆሜያለሁ ማለቱ ለይምሰል መሆኑን የሚያሳይ ሁነኛ የወሬ ሱሰኝነት ነው፡፡ ሁላችንም እንደምረዳው የግለሰቦቹ ወይም የማንኛውም በፍርድ ሂደት ውስጥ ያለ አካል ሰላማዊነት ወይም ወንጀለኝነት የሚረጋገጠው በህግና በህግ ብቻ ነው፡፡ ኃላፊነቱም የህግ ነው፡፡ የችሎት ሂደቱ ገና ቀጠሮ በተያዘበት ሁኔታ እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ በማለት የአንዲት ሉዓላዊት ሀገርን ህዝብ ጉዳይ መፈትፈት ትክክል አይመስለኝም– ንቀትም ጭምር ነው፡፡

የተቋሙ ስህተትና ድፍረት በህግ በተያዘ ጉዳይ ላይ ገብቶ መፈትፈቱና ለማሳሳት መሞከሩ ብቻ አይደለም፡፡ ተካሳሾቹ ለፍርድ የቀረቡት የእምነት ነፃነታቸው እንዲከበር በመጠየቃቸው መሆኑን አክሎ አቤቱታውን ለማጣፈጥ መውተርተሩ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ተቋሙ ያልነበረንና ያላየውን ሁሉ ማራገብ ግብሩ በመሆኑ ያስደመጠው ወሬ ብዙም የሚገርም አይደለም፡፡ ለምን ቢሉ፤ የኢትዮጵያን ሙስሊሞች የትናንት ዳራን አያውቅም ወይም እያወቀ ሆን ብሎ በመተኛቱ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን ተቋሙ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ለእምነት የታገሉ ምዕመናንን ታሰሩ ቢልም፤ ዕውነታውን የምናወቅ፣ የትናንት ኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ታሪክን አበጠርጥረን የምንረዳ ወይም በዘመኑ የኖረን መመስከር እንችላለን፡፡

የዘመኑ ኢትዮጵያ ሙስሊሞችም ይሁኑ የሌሎች እምነት ተከታዮች የአምልኮ ነጻነት ችግር ወይም የመንግስት ጣልቃ ገብነት ስጋት አለባቸው ቢባል በየትኛውም መስፈርት ቢመዘን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ዛሬ ሀገራችን የእምነት ነፃነትና የሃይማኖት እኩልነት ስፍኗል፡፡ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እየገባ የሚፈተፍትበት ዘመን አልፏል፡፡ እንዲህ ዓይነት ፍላጎትም የለውም። ፍላጎት ብቻም ሳይሆን መብትም የለውም– ህገ-መንግስቱ ይገድበዋልና፡፡ እናም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የተበደሉበት ወቅት ድሮ አክትሟል፡፡ ያኔ የገዥ መደቦች እምነት ተከታዮች የሆኑ ገነት የሚገቡበት፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ገሃነም ይገባሉ እየተባለ የሚሰበክበት የአፄው ዘመን እንዲሁም ሃይማኖት እንደ ውግዘት የሚቆጠርበት የአምባገነኑ መንግስቱ ስርዓት ዳግም ላይመለሱ ተሰናብተዋል፡፡ እናም ዛሬ አዲስ የአምልኮ ፀሐይ የወጣበት ቀን ነው። ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት እምነታችንን እንዳሻችን  የምንከውንበትም ነው– ምስጋና ይህን ነፃነት ለማምጣት ሲሉ የተሰው ውድ የህዝብ ልጆች ይሁንና። በመሆኑም መንግስት በእምነት ውስጥ ጣልቃ የሚገባበት ምንም ዕድል ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

ዳሩ ግን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ፣ ሃይማኖትም በመንግስት ተግባራት ውስጥ ጣልቃ አይገቡም ሲባል፤ በሃይማኖት ሽፋን ዜጎች ለስጋት ሲጋለጡና ሀገር አደጋ ላይ ስትወድቅ መንግስት እጁን አጣጥፎ እንደ ፊልም ይመለከታል ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የሂዩማን ራይትስ ዎች የወሬ ሱስ አለባልታም ከዚሁ አኳያ መታየት ይኖርበታል። እናም ሱሰኛው ተቋም የኢትዮጵያ መንግስት በእስልምና እምነት ተከታዮች ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ንጹሃን ዜጎችን ያለ አግባብ ለፍርድ ያቀርባል ቢልም፤ ሃቁ ግን ተቃራኒ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለእስር የተዳረጉት ተጠርጣሪ ግለሰቦች ህዝበ ሙስሊሙን የሚወክሉ ሳይሆኑ፤ አክራሪነትን ለማስፋፋት በተጨባጭ ሲንቀሳቀሱና አመፃን ሲሰብኩ የነበሩ የዋህቢያና የመጤ ሃይማኖት አቀንቃኞች ናቸው፡፡ በዚህም ተጠርጣሪዎቹ ኢስላማዊ መንግሰት ለመመስረት ያከናወኗቸውን ተግባራት ራሳቸው በአንደበታቸው የገለጿቸው ከመሆኑም በላይ፤ በልዩ ልዩ ሰነዶችና በዓይን እማኞች ጭምር የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አብዛኛው ህዝበ ሙስሊም ጉዳዮን በቅርበት እየተከታተለው ስለ ነበር ዕውነታውን የሚመሰክረው ነው፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ግለሰቦች የሚያቀነቅኑለት ዋህቢያ ዳራው ሲጠና የሚገኘው ውጤት ደም ደም የሚሸት የጥፋት ገፅ ነው፡፡ ዋህቢያ የሃይማኖት አክራሪነትን በመስበክና በማስፋፋት ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ አጀንዳን የሚያራምድ የጥፋት ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ ሃይማኖተኛም ፖለቲከኛም አይደለም፡፡ በሁለቱ ሃቆች መካከል ሰፍሮ፤ በሁለት ቢላዋ የሚበላ ፀረ -ሙስሊም ድርጅት ነው፡፡ ንፁሃንን ያርዳል፡፡ ሴቶችን ይደፍራል፡፡ የነባሩን እስልምና እምነት ተከታዮችን ይገድላል፡፡ ቤተ- እምነቶችን ያቃጥላል፡፡ በአጭሩ የማሊው አንሳር ዲን እና የናይጄሪያው ቦኮ ሃራም ዓይነት አክራሪነትን በይፋ ሲሰብክ የነበረ የጥፋት ማዕከልና አስተሳሰብ ነው፡፡

እነዚህ እኩይ ተግባራት ደግሞ ኢስላምንም ይሁን የኢትዮጵያን ሙስሊምን አይወክሉም፡፡ ኢስላም የሠላም፣ የአንድነት፣ የፍቅር የወዳጅነት ሃይማኖት ነው፡፡ አንድን የሰው ልጅ ህይወት ማጥፋት፣ የሰው ዘርን ከምድረ ገፅ የማጥፋት ያህል እንደሚቆጠር ቅዱስ ቁርዓን ያስተምራል፡፡ አንዳንድ ገራገሮች እንደሚገምቱት ሳይሆን፣ ጅሃድ ራሱ በእስልምና አስተምህሮት ያለ አንዳች ምክንያት የሚደገፍ አይደለም– በጥራዝ ነጠቅ ሃይማኖታዊ ነጋዴዎች ፍልስፍና እንጂ። ታዲያ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሙስሊም ይህን መሰሉን የዋህቢያንና የአጫፋሪዎቹን ቀኖና አምርሮ ይጠላል። በተለያዩ ጊዜያትም በሰላማዊ ሰልፍ ሳይቀር ተግባሩን ኮንኗል፡፡

እናም የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነኝ ባዩ ተቋም ለመሞገት የቆመላቸው ተጠርጣሪ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው ፍትህ እንዲያገኙ የተደረጉት፤ እምነቱና ቃሉ ከሚያዘውና ከሚፈቅደው እንዲሁም ህሊናም ሆነ ህግም ከማይቀበለው አስተሳሰብ ያፈነገጠ እኩይ ምግባር በመፈጸማቸው እንጂ ሙስሊሞች ስለሆኑ አይደለም፡፡ የግለሰቦቹ ጥያቄ የእምነት ጥያቄ ቢሆንማ መላ ህዝበ

ሙስሊም ከጎናቸው በተሰለፈ ነበር፡፡ ግን አላደረገውም፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ሠላም ወዳድ በመሆኑ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተሰልፎ እየተቃወማቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊም ጥፋትን፣ ወንጀልን፣ አክራሪነትን አጥብቆ ይጠላል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከማንኛውም የኋላ ዘመን ጋር ሲነጻጸር ምቹ የሆነ የእምነት ነጻነት ተሰጥቶታል፡፡

የሂዩማን ራይትስ ዎች ፍሬ ፈርስኪ መግለጫ በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ የከተማ የወሬ ቃርሚያዎችን እያለቃቀመ መንግስትን ማጠልሸት እንጀራው ነውና፤ ታሳሪዎች የህግ ምክርና አገልግሎት እንዳያገኙ፣ የፍርድ ሂደቱን ቤተሰቦቻቸው፣ ጋዜጠኞችና ዲፕሎማቶች እንደይከታተሉት አግዷል ሲልም ቀላምዷል፡፡

ይህ ፍፁም ዓይን ያወጣና ያገጠጠ አባባል ነው— የቅጥፈቶች ሁሉ ቅጥፈት። ለምን ቢሉ፤ ተጠርጣሪዎቹ የራሳቸውን ጠበቃ አቁመውና የህግ ምክር የሚሰጣቸው ባለሙያ ቀጥረው የፍርድ ሂደቱን በመከታተል ላይ በመሆናቸው ነው፡፡ የችሎት ሂደትም ቢሆን ለምስክሮች ግላዊ ደህንነት ሲባል ምስክር ማሰማቱ ሂደት ካልሆነ በስተቀር፤ ቀሪው ችሎት  ለቤተሰቦቻቸውም ይሁን ለሚዲያ ክፍት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ ተጠርጣሪዎቹ ነጻ ይሁኑም ወንጀለኛ መረጃዎችን መዝኖ የመወሰኑ ስልጣን የፍትህ አካሉ ቢሆንም፤ የችሎቱን ሂደት ግን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለምንም ገደብ ሊከታተለው ይችላል።

እናም የፍርድ ሂደቱ ለሚዲያና ለህብረተሰቡ በግልጽ የሚካሄድ መሆኑን ለመመስከር ብዙ መድከም አያስፈልግም፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ በየጊዜው የምንከታተለውን የሚዲያ ውጤቶች ማስተዋሉ ብቻ በቂ ነው፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች እንዳሻው የሚፈተፍተው ያላየውን በመሆኑ አይፈርድበትም፡፡ ጉዳዩ "በሌላው ምንትስ እንጨት ስደድበት" ዓይነት ነው፡፡ የተቋሙ ሥራ ያልተፈጠረን በመፍጠር የመንግስትንና የህዝብን ስምና ዝና በማጉደፍ ከለጋሽ ሃገራት ጋር ማላተም በመሆኑ፤ ለእሱ የሃቅ ጉዳይ ምኑም አይደለም፡፡  የሞራል ጥያቄም ውስጡ የለም፡፡ ዋናው ጉዳይ የያዘውን የውሸት ድንጋይ ማስወንጨፍ ብቻ ነው—ዒላማውን ቢመታም ባይመታም። ያም ሆነ ግን ይህ የፍርድ ሂደቱን ለመመስከር ከኛ ይልቅ ሂዩማን ራይትስ ዎች ለዜጎቻችን ቅርበት ያለውና ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት መሞከሩ አስቂኝ ድራማ ነው።

አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንንም ወቅሷል — ምን መውቀስ ብቻ ከሷልም እንጂ፡፡ ከፀረ -ሽብር ድርጊት ጋር የተያያዘውን "ጀሃዳዊ ሃረካት" የተሰኘውን ዘጋቢ ፊልም ማቅረቡን በማብጠልጠል። እግርጥ ነው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አሸባሪነትን የሚያወግዝ ትምህርታዊ ፕሮግራም አቅርቧል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የሚዲያ አንዱና ምናልባትም ዋነኛ ተግባሩ ማስተማር፣ ዜጎችን ካልተገባ ድርጊት መመለስና ስብዕናን ማረቅ ነው፡፡ እናም የቀረበው ዘጋቢ ፊልም ሀገራዊ ደህንነታችንን በተገቢው ሁኔታ መከላከል ካልቻልን ሊደርስብን የሚችለውን

አሳዛኝ ሁኔታ የሚያመላክት በመሆኑ ማለፊያ ስራ ነው ማለት ይቻላል። በክርስትናም ይሁን በእስልምና ስም ተጠልለው ፖለቲካዊ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚሯሯጡ ጥቂት ግለሰቦችን የመከነ ህልምን በሚገባ በማሳየቱም ቴሌቪዥኑ ሊመሰገን ይገባዋል። ምክንያቱም ሃይማኖትን እንደ ሽፋን በመጠለል የሚከናወኑ ተግባራትን ዕውነታ በአጉሊ መነፅር የቀረበ ያህል ፍንትው አድርጎ ስላሳየን ነው።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚሰራው እንደ አንድ ታዳጊ ሀገር ልማታዊ ሚዲያ ነው፡፡ የሀገራችንና የህዝቦቿ ፍላጎት ድህነትን ታሪክ ማድረግ እንደመሆኑ መጠን፤ ይህን ሂደት ለማሰናከል በፀረ-ሰላምነት ፊት ለፊት አሜኬላ እሾህ ሆነው የሚቆሙ ሃይሎችን ህዝቡ እንዲያውቃቸውና ከተግባራቸውም እንዲማር ማድረግ የሚዲያው አንድ ተልዕኮ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ከዚህ በተጨማሪም ቴሌቪዥኑ ያቀረበው ጉዳይ ከአል-ሸባብና ከአል-ቃዒዳ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሀገርን ከጥፋት ተልዕኮ የማዳን ተግባር እንጂ፤ ያለ አንዳች ግንዛቤ በደፈናው ከግለሰቦች መብት መጣስ ጋር ማገናኘት አግባብነት የጎደለው ዕይታ ነው። ስለሆነም ፀረ - ሠላም እንቅስቃሴዎችን ማውገዙ የሚያስወድሰው እንጂ የሚያስወቅሰው አይመስለኝም፡፡ ይህ በየትኛውም ዓለም የሚሰራበት ሃቅ ነው፡፡ ሂዮማን ራይትስ ዎች ራሱ የሚያውቃቸው እንግሊዛዊንም ሆኑ አሜሪካዊያን የሚዲያ ተቋማት መሰል ክንዋኔዎችን ይዘግባሉ፡፡ ታዲያ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይህን ተግባር መዘገቡ አዲስ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?...

ስለሆነም ዘጋቢ ፊልሙ ዜጎች የአሸባሪነትን አደጋ እንዲገነዘቡና ራሳቸውን ከጥፋት እንዲታደጉ እንደ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ታላላቅ የዓለማችን መገናኛ ብዙሃንም ቢሆኑ ብሔራዊ ስጋቶችን ከርቀት ማስቀረት የሚችሉ የህትመትና የብሮድካስት ሚዲያዎችን በስፋት የሚጠቀሙ በመሆናቸው፤ የኢቲቪ ዘጋቢ ፊልም እንደ ወንጀል ተቆጥሮ የመግለጫ ጥራዝ ዳጎሰ እንዲል በግብዓትነት መቅረብ የለበትም ባይ ነኝ፡፡ እናም ጉዳዩ ሂዩማን ራይትስ ዎች እንደሚያራግበው ፊልሙ የፍርድ ሂደቱን ለሚያዛባና የግለሰቦችን መብት የሚጋፋ ሳይሆን፤ የህብረተሰቡንና ብሔራዊ ደህንነት ለመጠበቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የፍርድ ሂደቱ የሚዳኘው በህግና በሥርዓት ነው፡፡ በአንድ ወገን የስሜት ማዕበል ወዲያና ወዲህ የሚናወጥ የውኃ ላይ ኩበት አይደለም፡፡ የዳኝነት ስርዓቱን አንዳንድ ሃላፊነት የማይሰማቸው ሚዲያዎች ምንም ይበሉት ምን፤ ተጠርጣሪዎችን ነጻ አሊያም ወንጀለኛ የሚያደርጋቸው ህጉና ህጉ ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ሌስሌ ሌፍኮ የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ኃላፊ ነው፡፡ ከአክራሪ ኒዮ - ሊበራሊስቶች ባንክ ሂሳብ ቁጥር ረብጣ፣ ረብጣ ዶላር የሚንዥረቀዥረቅለት የፖለቲካዊ -ኢኮኖሚ ድርጅት አቀንቃኙ፤ በድረ - ገጹ ባሰራጨው ተመሳሳይ ዘገባው የአሳዳሪውን ፈለግ አጠናክሯል፡፡

ጉዳኛ የእኩይ ደቀ- መዝሙር ነው፡፡ ሰውዬው በሰላማዊ መንገድ ሁሉ የሚቃወሙትን አፍ ለማዘጋት የፀረ - ሽብር ህግ ማውጣቱ ህግን ከማዛባት የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም ሲል በድፍረት ጽፏል–የኢትዮጵያን መንግስት መሆኑ ነው፡፡

በመሰረቱ የፀረ - ሽብርተኝነት ህግ ማውጣትና ወንጀለኞችን ለህግ ማቅረብ የዜጎችን መብት ከማፈን ጋር የሚያስተሳስረው አንዳችም ነገር የለም፡፡ መንግስት እንደማንኛውም ሀገር መንግስት ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ልዩ ልዩ አዋጆችንና ህጎችን የማርቀቅና ወደ ስራ የመተርጎም መብትም ግዴታም አለበት፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም የነባራዊው ዓለም ተጋሪ በመሆኑ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን ማውጣቱና በስራ ላይ ማዋሉ ሊደንቅ አይገባም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የወጣው የፀረ - ሽብር ህጉ ዜጎችን ከማንኛውም ሰላማዊ እንቅስቃሴ ገትቷል የሚለው ግን በፍጹም ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አሁንም እንዳሻቸው የሚጽፉና የሚናገሩ ህግና ሥርዓቱን ተከትለው ሰላማዊ ሰልፍ የሚያደርጉ አያሌ ዜጎች በመኖራቸው ነው። የዚህ ፅሑፍ አጀንዳ ባለመሆኑ እንጂ ከዚህ አኳያ በርካታ አብነቶችን መጠቃቀስ ይቻል ነበር፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎች መንግስትን ከማብጠልጠሉ በዘለለም ግልጽ የሆነ ጣልቃ ገብነቱንም በመግለጫው ላይ አስቀምጧል፡፡ የማን አለብኝ ባዩን አክራሪ ተቋም አባባልን ቃል በቃል ልዋስና "…የኢትዮጵያ መንግስት የፀረ - ሽብር ህጉን እንደገና ሊያሻሽለውና ፖለቲካዊ ተነሳሽነት ያላቸውን ክሶች ከማቅረብ ሊቆጠብ ይገባዋል" በማለት ማስፈራሪያ ይሁን ምክር ቢጤ ያልለየለት መልዕክት ጣል አድርጓል፡፡ በሰው ሀገር ውስጥ ጣልቃ በመግባት ጡንቻውን የተማመነ ዓይነት ተቋም ሳይሆን የቀረ አይመስለኝም፡፡ ግና የሁል ጊዜ ዘፈኑ በመሆኑ አይደንቀንም–ከማውራት ውጪ አንድ እርምጃም ወደፊት አይሄድም።

ሁላችንም እንደምንረዳው በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት የበለጠ ወንጀል የለም– ተቋሙ የራሱ ጥፋት አይታየውም እንጂ። እርግጥ ፍላጎቱ ኢትዮጵያዊን ጥቁሮች ስለሆኑ ምንም አያውቁና እናስተምራቸው ከማለት የመነጨ ዕብሪተኝነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የሚበጀንን የምናውቀው እኛ ነን። እኛ ኢትዮጵያኖች ለራሳችን ከማወቅ አልፈንም ለጎረቤቶቻችንም የተረፍን ነን። ዓለም ያመነብን የፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ባለቤቶችም ጭምር።….እናም ከእኛ ወዲያ ለእኛ ላሳር እነደሆነ ተቋሙ ሊያውቀው ይገባል።

ያም ሆነ ይህ ግን ተቋሙ የራሱ ድብቅ አጀንዳ አለውና ያሻውን በፈለገው መንገድ ይበል ብለን ብንተወው እንዲሁም ከንቱ ምክሩን ከተራ ጉዳይ ቆጥረን ልንረሳው ብንችልም በሬ ወለደ ክሱን ግን መታገስ አይቻልም–የሀገር ጉዳይ ነውና እንደ ዜጋ ሃቁን መንገር ያስፈልጋል። በመሆኑም እርሱ እንዳለው ጋዜጠኞች በፃፉት ፅሑፍ አልታሰሩም፡ የታሰሩት በወንጀለኝነታቸው ነው፡፡ የታሰረት ከሀገሪቱ ህግና ስርዓት ውጪ ሲሰሩ የነበሩ የጥፋት ተባባሪ የሚዲያ ሰዎች

ናቸው፡፡ በመሆኑም ወንጀለኞችን የህግ ተጠያቂ ማድረግ የህግ ጥሰት አይደለም፡፡ ደግሞም አንድ ሰው ጋዜጠኛ ስለሆነ ከተጠያቂነት እንደማይድን ግልፅ ነው፡፡ ጋዜጠኛም ይሁን አራሽ፣ ቀዳሽም ይሁን ተኳሽ ህግን እስከተላለፈ ድረስ መጠየቁ አይቀሬ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩም አክራሪው ተቋም እንደሚወተውተው ጉዳያቸው በህግ እንዲታይ የተደረጉ ግለሰቦችም ቢሆኑ የክሳቸው መነሻ ሙስሊም መሆናቸው አይደለም፡፡ የኢስላም፣ የክርስትና አሊያም የሌላ ሃይማኖት ተከታይ መሆን አያስከስስም፤ ህግን ከተላለፈም ነጻ አያደርግም፡፡

የተቋሙ የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ኃላፊ ፀረ - ኢትዮጵያዊ ዘገባ ረዘም ያለ ነው፡፡ ምክትል ሃላፊው ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ኢትዮጵያ ግልጽ የሆነ የደህንነት ስጋት እንዳለባት በይፋ ከተናገሩ በኋላ፤ የኢትዮጵያ መንግስት የፀረ - ሽብርተኝነት ህጉን በሚዲያ፣ በፖለቲካ ተቃዋሚዎችና በቅርቡ ደግሞ በተቃውሞ ሰልፍኞች ላይ መጠቀሙ የለየለት ህግን ያለ አግባብ የመጠቀም እንዲሁም ፍትህን የመጣስ ድርጊት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ …እኔ በበኩሌ ይህን አባባል የተምታታና የለየለት ድፍረት ብየዋለሁ፡፡ ሰውዬው በአንድ በኩል ሀገራችን በስጋት ቀጣና ውስጥ መሆኗን ይናገራሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጠበቅ ያለ ህግ ማውጣቷን ይቃወማሉ– ሁለት የማይጣጣሙ አባባሎች። ይህ ደግሞ ከአንድ ለሰብዓዊ መብት መረጋገጥ ቆሚያለሁ ከሚል ተቋም የማይጠበቅ ምናልባትም ብስለት የጎደለው ድምዳሜ ነው፡፡

በጥቅሉ ሂዩማን ራይትስ ዎች ሀገራችን በጥፋት ኃይሎች መከበቧን ባመነበት ምላሱ ዜጎቿን ሉዓላዊነቷን የሚታደግለት ህግና ሥርዓት ማበጀቷን ለምን እንደሚያጠጥሉት አይገባኝም፡፡ ምናልባትም ኢትዮጵያን የማብጠልጠል የሱሰኝነቱ ወረፋ ደርሶበት ይሆናል። ግና አክራሪው ተቋምም ይሁን ሰዎቹ ምንም ይበሉ ምን፤ መንግስት ዜጎቹን የመጠበቅ መብትም ግዴታም ስላለበት በህዝቡ ተወካዮች አማካኝነት ያፀደቀውን የፀረ - ሽብር ህግ ከመተግበር የሚያግደው አሰራር የለም፡፡ እናም ሱሰኛው ፀረ - ኢትዮጵያ ተቋም የቱንም ያህል የሀገራችንን ስም በበሬ ወለደ መግለጫው ለማጠልሸት ታችም ቢወርድ፣ ላይም ቢወጣም የጀመርነው የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ግስጋሴያችን ለደቂቃም ቢሆን አይገታም፡፡ መቼም ቢሆን…